የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት
The Coalition of Ethiopian Opposition Political Organizations (CEOPO)

CEOPO, Postfach 102409, 60024 Frankfurt-Germany, e-mail CEOPO@T-Online.de
Tel./Fax/+496937108840,+496937108252

# የኢተፖድህ አስተባባሪ ኮሚቴና የህብረቱ የአገር ውስጥ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጋራ ስብሰባ ግንዛቤዎችና ውሳኔዎች፤

የኢተፖድህ አስተባባሪ ኮሚቴና የህብረቱ የአገር ውስጥ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጋራ ስብሰባ የካቲት ፭ እና ፮ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. በፍራንክፈርት ከተማ ተካሂዶ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል::

ይህ ስብሰባ የተካሄደበት ወቅት ሀገራችን ከብዙ አቅጣጫ የተጋረጡባት ነባርና አዳዲስ ችግሮች የተፋፋሙበትና ተቃዋሚ ኃይሎች ኅብረታቸውን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አጠንክረው እየተነሳሳ ያለውን የህዝብ ትግል አመራር ለመስጠት እጥፍ ድርብ ጥረት እንዲያደርጉ በሚጠይቅ ወቅት ነው::

በአንድ በኩል ነባር ችግሮቻችን አሉ:: የወያኔ /ኢህአዴግ ፖሊሲ ከመሻሻል ይልቅ እንዲባባስ ያደረገው ረሃብ ከስምንት ሚሊዮን የሚበልጡ ወገኖቻችንን ከፍተኛ ችግርና እንግልት ላይ ጥሏቸዋል:: በሸዓቢያ ዕብሪተኛ ወረራ ምክንያት የሃገራችን ሉዓላዊነትና ኅልውና ተደፍሮ ይህንን አደጋ ለመቋቋም በደርዘን ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ሕይወታቸውን ቢሰዉም አሁንም አደጋው አፍጥጠ ና አግጠ እንዳለ ነው:: በአንዳንድ ባዕዳን አይዞህ ባይነት ዕብሪቱ የጨመረው የሻዕቢያ አገዛዝ አሁን ም በኃይል ከያዛቸው ግዛቶች ወጥቶ ችግሩን በውይይት ለመፍታት ፈቃደኛነት ባለማሳየቱ የኢትዮጵ ያም ሆነ የኤርትራ ሕዝቦች ላይ አሳዛኝና አሰቃቂ ጦርነትና ፍጅት ደመና እያንዣበበብን ይገኛል::

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ነባር ችግሮች ለመቋቋምና ለመፍታት እንዲቻል ወያኔ /ኢህአዴግ ህብረ ተሰቡን አረጋግቶና አስተባብሮ መምራት የሚጠበቅበት አገዛዝ ይባስ ብሎ ይበለጥ አለመረጋጋትና መቃቃርን በሚፈጥሩ አስጸያፊና ጸረ ሕዝብ ተግባራት ላይ በመሰማራት አዳዲስ ችግሮች እየተጋረጡ ብን እንገኛለን::

ዞሮ ዞሮ ወያኔ /ኢህአዴግ እራሱ እስከ አዘጋጀውና፥ እራሱ እስከተቆጣጠረው ድረስ አሸነፍኩ ብሎ ከሚወጣበት ምርጫ እንኳን ዜጎች እንወዳደራለን ብለው መመዝገባቸውና፥ ሌሎች ዜጎች ደግሞ እነዚህን ተወዳዳሪዎች እንደግፋለን ብለው መንቀሳቀሳቸው እንኳን ለወያኔ መሪዎች የማይዋጥ ክስተት ሆኖባቸው ከጥቂት ሳምንታት ወዲህ በተወዳዳሪዎችና በደጋፊዎቻቸው ላይ ይህ ነው የማይባል የእስራት፥ የማስፈራራት፥ የግድያና የአፈና ውርጅብኝ በማካሄድ ላይ ናቸው:: ለሕዝብ መብት ለመስጠት ሳይሆን ሕዝብን ለመከፋፈል በቀየሱት ዘረኛ አገዛዝ ሳቢያ የወላይታ ሕዝ ብ ይከበርልኝ ብሎ መብቱን መጠየቁ እንደ ድፍረት ተቆጥሮበት ከፍተኛ የጭቆና ዘመቻ እየተፈጸ መበት ይገኛል::

የወያኑ አገዛዝ ስለግንቦት ምርጫ ውጤት ምንም የሚጨነቅበት ነገር ባይኖርም በሱ ሳቢያ በመካሄድ ላይ ያለው የሕዝብ ለትግል የመነሳሳት መንፈስ ከተጠበቀው በላይ ሆኖበት ከፍተኛ ውጥረት ላይ እንዳለ ግልጽ ነው:: የወያኔን ካድሬዎች የአፈና፥የእስራትና የግድያ ዘመቻ ከምንም ሳይቆጥሩ በሃገሪ ቱ የተለያዩ ክፍሎች ዜጎች በድርጅትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ለመወዳደር ተመዝግበዋል:: ሕጉ በሚ ጠይቀው መሰረት ለተወዳዳሪነት ለመመዝገብ የድጋፍ ፊርማ በማስፈለጉ እነሱ እንደዚሁ የወያኔ ካ ድሬዎችን ሕገወጥና ጸረ ሕዝብ ውርጅብኝ ተቋቁመው በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ለተቃዋሚዎች የድጋፍ ፊርማቸውን ሰጥተዋል:: ይህ ሁኔታ በፈጠረው መደናገጥ መረን የተለቀቁ ካድሬዎች ባደረሱት ጥፋት የብዙ ሀቀኛ ዜጎች ሕይወት አልፏል::ብዙዎችም ከኑሮአቸው ተፈናቅለዋል:: አሁን ም ዜጎች እየታገሉና እየተሰዉ ናቸው::

ይህ በመካሄድና በመፋፋም ላይ ያለው ትግልና በመከፈል ላይ ያለው የሕዝብ መንገላታትና መስዋዕትነት ጥቂቶችን ምንም ለማይፈይዱበት የፓርላሜንት ወንበሮች ለማብቃት የሚደረግ ትግልና የሚከፈል መስዋዕትነት አይደለም::በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ÷ፍትህና ዘላቂ ሰላም የሚደረገውና መደረግም ያለበት የረዥም ጊዜ ተጋድሎ አንድ አካል ነው:: በመሆኑም ወያኔ በወሰነው የጊዜ ገደብ ታጥሮ ግንቦት ላይ እንዳያከትም÷ የሕዝባችን የዴሞክራሲ÷የሰላም የፍትህ ጥማቶች በሕዝባዊ ትግል ሕዝባዊና ፍትሐዊ ምላሽ እስኪያገኙ ድረስ እየሰፋ÷ እየጠነከረና እየተባበረ እንዲቀጥል የሃገራችን ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች በሙሉ ከፍተኛ ሕዝባዊ አደራ እንደተጣለባቸው መረዳት ይኖርባቸዋል::

በግንቦቱ ምርጫ የተወሰኑ ተቃዋሚ ዜጎች የተወሰኑ የፓርላሜንት ወንበሮች በወያኔ መልካም ፈቃድ ያገኙ ይሆናል:: ነገር ግን ዛሬ በወላይታ ሆነ በሃድያ÷ በአዲስ አበባ ሆነ በጎንደር÷ በሐረር ሆነ በባሌ ሕዝባችን በማካሄድ ላይ ላለው ትግል መነሻና ምክንያት የሆኑት መሠረታዊ የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ብን ብለው አይጠፉም::

ወያኔ/ኢህአዴግ በተጭበረበረ የምርጫ ሂደቱ አገኘሁ በሚለው ሕዝባዊ ቅባሎት ስለሚኩራራ እነዚህ ችግሮች ሕዝባችንን አላስቀምም አላስቀመጥ በሚል አስከፊ ገጽታቸው ተባብሰው ይቀጥላሉ:: የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ዛሬ በዓይናቸው ሥር እየተወለደ ያለውን የትግል አዲስ እመርታ ምንነት ተገንዝበው ቀጣይነት እንዲኖረውና ተባብሮ እንዲፋፋም የጋራና የግንባር ቀደም አመራር ለመስጠት ከቻሉ የሕዝባችን መስዋዕትነት ፍሬ አፍርቶ ፍትህና የህግ የበላይነት የሚረጋገጥበት ብሩህ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ ይፈጠራል::

ይኼንን እየተነሳሳ ያለውን የሕዝባችንን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚደረግን ትግል የመምራት ኃላፊነት ያለባቸው ተቃዋሚ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች በሆነ ባልሆነው እየተናቆሩ ይህንን ብሔራዊ አደራ መወጣት ካቃታቸው በግፍ አገዛዝ የተንገፈገፈው ሕዝባችን ከአልሞት ባይ ተጋዳይነት ግፊት ለሚፈልቁ ግብታዊ ፍንዳታዎች ተዳርጎ÷ በየፊናው ተራ በተራ እየተነሳ ተራ በተራ እየተመታ ሃገራችን ወደ ባሰ ትርምስ÷ ወደ ዘግናኝ የመከራ ዘመን ጉዞዋን ትቀጥላለች::

የኢተፖድህ ስብሰባ የሃገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ ከዚህ አንጻር በዝርዝር ከተመለከተ በኋላ በአሁኑ ወቅት ከወያኔ/ኢህአዴግ ግፍ ማየል ጋር እየተፋፋመ በመሄድ ላይ ያለው ትግል ይበልጥ እንዲቀነባበርና ቀጣይነትም እንዲኖረው በዝርዝር ነጥቦች ላይ ያስተላለፍናቸውን ዋና ዋና ውሳኔዎች እንደሚከተለው እናቀርባለን::

## ክፍል አንድ

## በተቃዋሚ ድርጅቶች መሃከል ስለተፈጠሩ ያካሄድ ልዩነቶች

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተቃዋሚነት ጎራ በተሰለፉት ታጋዮች መሃከል የተከሰቱት ልዩነቶች በጋራ ውይይትና በመቻቻል የጋራ ትግሉን በሚያግዝ ሁኔታ ሊፈቱ ባለመቻላቸው ለወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ የልብ ልብ ሰጥቶ ሕዝባችንን ለባሰ ጥቃት ዳርጎታል::ከዚህም በተጨማሪ የታጋዮችን መንፈስ የረበሸና የትግል ወኔ ያቀዘቀዘ÷ለትግል የተነሳውንም ሕዝብ የጋራ ግንባር ቀደም አመራር እንዳያገኝ ያደረገ መሆኑ ግልጽ ነው:: ኢተፖድህ ከዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ለመውጣት የተቻላውን ጥረት እያደረገ በጋራ በተቀየሰው የትግል መስመሩ ለአገርና ለወገን የገባውን ቃልኪዳን ሳያጥፍ ትግሉን ይቀጥላል:: በዚህ ትግላችንም የሃገራችን ዴሞክራቶች በሙሉ በዚህ ጥረታችን ከጎናችን በመቆም እንዲተባበሩን ጥሪያችንን እያቀረብን ለህብረት ትግሉ ጠንክሮ አለመውጣት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ድርጅቶች ደግሞ ሕዝባችን ዛሬ ከእኛ የሚጠብቀው የጋራ ትግልን እንጂ መከፋፈልን እንዳልሆነ ተገንዝበው ህብረታችንን ለማጠናከር ከልብ እንዲሰሩ ይጠይቃል::ከዚህም በመነሳት፤

፩ኛ/ በአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ውስጥ ስለተከሰተው ውዝግብ

ይህ ውዝግብ በተለይ ዛሬ ሕዝባችን በየአቅጣጫው ለትግል እየተነሳሳና እየተሰዋ ባለበትና የጋራ አመራር በሚጠይቅበት ወቅት የተከሰተ በመሆኑ ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል እጅግ የጎዳ ውዝግብ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ በተቃዋሚዎች መሃከል የሚነሱ ማናቸውም ችግሮች በዚያው በተቃዋሚዎች ሠፈር በውይይትና በመግባባት የመፈታታቸውን ጉዳይ ቅድሚያ ሳይሰጡ የእራሱ የተለየ አጀንዳ ባለው የወያኔ /ኢህአዴግ መንግሥታዊ ተቋሞች አማካይነት ለወያኔ/ኢህአዴግ በሚያመች ሁኔታ ብቻ መፍትሄ በሚሰጡ ክፍሎች ችግሩን ለመፍታት ጥረት ማድረግ ኢተፖድህንም ሆነ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን የሀገራችንን ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ያሳዘነ አካሄድ ሆኖ አግኝተነዋል::

ኢተፖድህ ከዚህ ይልቅ ሁለቱም ወገኖች ችግራቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ወደ ፊት በሚያራምድ መልክ እንዲፈታ አሁንም ጥረታቸውን መቀጠል አለባቸው ብሎ ያምናል::ይህ ካልሆነና ሶስተኛ ወገን ካስፈለገ ችግራቸውን ለኢተፖድህ ወይም ህብረታችን ለሚሰይመው የሽምግልና ኮሚቴ ለማቅረብና የሁሉም ወገኖች ክርክሮች ታይተው ለሚሰጠው መፍትሄ ተገዥ እንደሚሆኑ እስከ አረጋገጡ ድረስ ኢተፖድህ ይህንን ጥያቄ ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል::

፪ኛ/ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብረት ከኢተፖድህ እራሱን ስለማግለሉ፤

የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብረት ከኢተፖድህ እራሱን ማግለሉና በዴሞክራሲያዊ አሰራር በሙሉ ድምጽ የተላለፈውን የህብረቱ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች አልቀበልም በማለት የተናጠል ጉዞ መቀጠሉ በህብረት የተጀመረውን የተባበረ የተቃዋሚ ኃይሎችን ትግል የጎዳ እርምጃ መሆኑ ግለጽ ነው:: በህብረቱ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉትን ልዩነቶች የህብረት ትግሉን በሚያግዝ መልክ ለመፍታት ኢተፖድህ ብቃት ያለው የዴሞክራሲ አሠራር የሚከተል የጋራ የህብረት ተቋም እንደመሆኑ መጠን ደኢህዴህ የያዘውን አቋም አስተካክሎና በዴሞክራሲ አሰራር በጋራ ለሚወሰዱ አቋሞች ተገዥነቱን አረጋግጦ ህዝባችን በተስፋ በሚጠብቀው የተባበረ የተቃዋሚ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች የህብረት መድረክ እንዲመለስ ጥሪ እናደርጋለን::

፫ኛ/ የኢትዮጵያ ህገራዊ ጉባዔን በሚመለከት፤

**ኢህጉ** የሲቪክ እንቅስቃሴ እንደመሆኑ መጠን ተልዕኮው የሃገራችን ዴሞክራቶች ደክመውና ጥረው የጋራ ትግል ለማካሄድ የፈጠሩትን ህብረት የማጠናከር እንጂ ኢተፖድህን አፍርሶ አዲስ ህብረት ምስረታ ሂደት ውስጥ መግባት አይጠበቅበትም::
እንዲህ ዓይነቱ ሂደት የኢትዮጵያን ሕዝብም ሆነ ታጋይ ኃይሎችን ለውዥንብር የሚያጋልጥ በመሆኑ ኢተፖድህ በመስከረም ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በፍራንክፈርት ከተማ ባካሄደው ጠቅላላ ጉባዔ እንደማይቀበለው በሙሉ ድምጽ አጽድቋል::
ህብረተሰባችን በተከታታይ በታላቅ ትዝብት የተመለከታቸውን በየጊዜው የተፈጠሩ የህብረት ስብስቦች ተፈጠሩ በተባለ ማግሥት የመፍረሳቸውና በሌላ የመተካታቸው ዜና የሰለቸው ስለሆነ ይኼንን የህዝባችንን የትግል ስሜት የሚያዳክም አዙሪት እንዲያበቃና የተፈጠረው ህብረት የበለጠ እንዲጠናከር አባል ድርጅቶችም ሆኑ ሌሎች የሲቪክ እንቅስቃሴዎች የበለጠ የኃላፊነት ስሜት በመላበስ ለህዝባዊ ትግሉ መጎልበት ለተባበረ የህብረት ትግል መቀጠል ገንቢ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ኢተፖድህ በድጋሚ ጥሪ ያደርጋል::

**ኢህጉም** በመስከረም ወር በፍራንክፈርት ከተማ በኢተፖድህ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት ተቃዋሚ ኃይሎችን ሊከፋፍሉ ከሚችሉ እርምጃዎች ተቆጥቦ እንደ ሲቪክ ተቋምነቱ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ላቋቋሙት ህብረት(ኢተፖድህ) ገንቢ ሂስና ድጋፍ እየሰጠ ይህንን የጋራ የተቃዋሚ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የህብረት መድረክ እንዲያግዝ ጥሪ እናደርጋለን::

## ክፍል ሁለት

## ኢተፖድህን ስለማጠናከር

ዓላማ ነው። ይህ የጋራ ሕዝባዊ ዓላማ ደግሞ ግቡን እስካልመታ ድረስ ትግሉ ከዕለት ዕለት እያየለ የሚሄድ መሆኑ የዚያኑ ያህል ግልጽ ነው።ከዚህ በመነሳት እስከ ግንቦትም ሆነ ከዚያ ባሻገር ለሚያካሂደው ትግል የኢተፖድህ መጠናከር ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው፤ ይህ ትግል በመጭው ጊዜ በሰፋፊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች፥ በሰላማዊ ሰልፎች፥ በሥራ ማቆም አድማዎች በመሳሰሉት የትግል ዘዴዎች እንዲታገዝ አስፈላጊው የፖለቲካ፥ የአወቃቀር፥ የፋይናንስና የቁሳቁስ ዝግጅት ከአሁኑ መደረግ እንዳለበት እሙን ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የህብረታችንን የእድገት ሂደት ለማጎልበት፤

፩ኛ/ ኢተፖድህ ለቆመላቸው አገራዊና ሕዝባዊ ዓላማዎች በውጭም ሆነ በሃገር ውስጥ የተለያዩ የፖለቲካ ፕሮግራሞችን በመያዝ የተደራጁ በተለያዩ ምክንያቶች የህብረት ትግሉን(ኢተፖድህን) ያልተቀላቀሉ ተመሳሳይ ዲሞክራሲያዊ ራዕይ ያላቸውና "<u>ህብረት ኃይል ነው</u>" የሚለውን መርህ የሚቀበሉ ኢትዮጵያዊ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ኢተፖድህን እንዲቀላቀሉ ጥሪ እናደርጋለን።

፪ኛ/ በውጭ አገር የሚገኙ የኢተፖድህ የድጋፍ ኮሚቴዎች የበለጠ ተጠናክረው የሚሰጡትን ሂሳዊ ድጋፍ እንዲቀጥሉ ለማስቻል የህብረቱን ዓላማዎች የሚደግፉትን ወገኖች በበለጠ በማሰባሰብ ቀጣይነት ባለው ዘዴ እንዲጠናከሩ የሚቻለው ጥረት እንዲደረግ ጥሪ እናደርጋለን።

፫ኛ/ በሀገር ውስጥ ብዙ በድርጀት ያልታቀፉ ዜጎች ህብረቱን ለማጠናከርና የህብረት ትግሉ የሚታገልላቸውን ዓላማዎችን ከኢተፖድህ ጎን በመሰለፍ ለመወጣት በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችና በቀጥታም በአገር ውስጥ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የቀረቡ የዜጎችን ጥያቄዎች ለማስተናገድ ይቻል ዘንድ በቅርቡ በኢተፖድህ ሰክሬታሪያት ዜጎችን ሊያሳትፍ የሚችል የአደረጃጀት ዘዴ ይቀየሳል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

### <u>ስለ መጭው ምርጫ</u>

ስብሰባው የኢተፖድህ ጠቅላላ ጉባዔ የግንቦቱን ምርጫ አስመልክቶ በመስከረም ወር ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች አሁንም ትክክለኛና ለትግሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ተገንዝቦ ተግባራዊ ስለሚሆኑበት ዘዴ በሰፊው ተወያይቷል።በዚህም መሠረት

፩ኛ/ ተቃዋሚ ኃይሎች ለብሔራዊ ዕርቅ፥ ለነጻና ርትአዊ ምርጫ የጀመሩትን ትግል እስከ ግንቦቱም ሆነ ከግንቦትም ባሻገር ቀጣይነት ሊኖረው በማችል መልኩ እንዲያፋፍሙና እንዲያቀናብሩ፤

፪ኛ/ ብሔራዊ ውይይትና እርቅን አሻፈረኝ በሚለው የወያኔ/ኢህአዴግ ገታራ አቋም ሳቢያ የሃገራችን ለባለ አለመረጋጋትና የጦርነት ቀውስም ውስጥ እንዳትገባ ገዥው ድርጅት ይህንን ጥሪ በአስቸኳይ እንዲቀበልና ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚከተለው ማንኛውም ችግር ከተጠያቂነት እንደማያመልጥ እያስገነዘበ ህዝቡ ትግሉን እንዲያፋፍም ጥሪ እናደርጋለን!

፫ኛ/ በግንቦቱ ምርጫ ሳቢያ በዕጩዎችና በደጋፊዎቻቸው ላይ የሚደረገውን የአፈና፥ የግድያ፥የእስራትና የማዋከብ እረምጃ ሙሉ በሙሉ እንዲቆም፤ በወላይታ በሃድያና በሌሎች አካባቢዎች በመፈጸም ላይ ያሉት የግፍ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲቆም አጥብቀን እናሳስባለን፤

፬ኛ/ በምርጫው ሳቢያም ሆነ ሰሞኑን በወላይታና በሃድያ በተፈጠረው ችግር ምክንያት በወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬዎቸች የተፈጸመውን ዕልቂት እያወገዝን በተፈጠረው ችግር ምክንያት የታሠሩ ዜጎች በሙሉ እንዲፈቱ፥ ከሥራቸው የተፈናቀሉ በሙሉ ወደ ስራቸውና ወደ ሰላማዊ ኑሮአቸው እንዲመለሱ አጥብቀን እንጠይቃለን።

፭ኛ/የፖለቲካና የህሊና እስረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፥ በዘፈቀደ ሕዝብን የማሰርና የማንገላታት ተግባር የሚፈጽሙ የወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬዎችም ሆኑ ሌሎች ባለሥልጣናት ለፍርድ እንዲቀርቡ፤

<u>፮ኛ/ ከአንድ እስከ አምስት ለተጠቀሱት ጥያቄዎች ተግባራዊነት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ</u> አገር

የጋራ ተቃውሞዎችና እንቅስቃሴዎች እንዲደረጉ ጥሪ ያደርጋል::

## ክፍል አራት

### በኢትዮጵያ የተከሰተውን ድርቅና ረሃብ በተመለከተ

ለዘመናት አገራችንና ሕዝባችንን ከሚፈታኑት መሰረታዊ ችግሮች አንዱ የሆነው ድርቅና
ረሃብ ዛሬም እንደ ትላንቱ ለበርካታ ወገኖቻችን እንደ ቅጠል መርገፍ መሰደድ ምክንያት እየሆነ ነ
ው:: ጦርነቱ÷ በሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ መንግሥት በሚከተለው የተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት የተ
ረጋጋ ማህበራዊ ሥርዓት ባለቤት መሆን ያልቻለው ወገን ከቁየውና ከኑሮው እየተፈናቀለ የችግሩን
ሁኔታ የበለጠ አባብሶታል:: በአገራችን የተከሰተው ድርቅ ዱብ ዕዳ ሳይሆን አዝጋሚ ተፈጥሮአዊ ክ
ስተቶችና በወቅቱ እየተከሰተ ያለውን አስጊ ሁኔታ ለመቆጣጠር በወያኔ/ ኢህአዴግ መንግሥት ሊደ
ርስ የሚችለውን አደጋ ለመከላከል እርምጃ ባለመውሰዱ÷ገበሬው በማዳበሪያ ዕዳ በመያዙ በሬውን ሸ
ጦ ለመክፈል በመገደዱና አምራች የገበሬው ኃይል ወደ ጦርሜዳ በመወሰዱና ወዘተ ......የመሳሰሉት
ምክንያቶች ችግሩን ሁኔታ አባብሶታል:: የኢተፖድህ አስተባባሪ ኮሚቴ የተባበሩት መንግሥታት
ይኼንን ችግር ለመቅረፍ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እየወሰደ ያለውን እርምጃ ከልብ እያደነቀ ጥረቱ አሁ
ንም የበርካታ ወገኖቻችን ሕይወት አደጋ ላይ ከመውደቁ በፊት ዓለም ዓቀፉ ሕብረተሰብ ይኼንን አ
ጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ለመለወጥ የሚቻለውን እርዳታ እንዲያደርግ ጥሪውን ያቀርባል::

በተጨማሪም የበርካታ ወገኖቻችን ሕይወት ለማትረፍ የሚከተሉት ልዩ ትኩረት እንዲሰጣቸው ኢተ
ፖድህ አጥብቆ ያሳስባል::

ሀ/ በድርቁ የተጎዱ ወገኖች ካለምንም አድልዎ የተገኘው እርዳታ እንዲታደላቸው እንዲደረግ÷

ለ/ ለእርዳታው ማከፋፈልና ማሰራጨት የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች
እንደ ልባቸው ተንቀሳቅሰው ካለምንም ተጽዕኖ እርዳታውን ማከፋፈልና ማሰራጨት እንዲችሉ
ማስቻል፤

ሐ/ በውጭ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ኮሚቴዎችን በማቋቋም ገንዘብ÷ ቁሳቁሶችን
በማሰባሰብ ልዩ ዘመቻ እንዲያካሂዱ ፤

መ/ ዓለም ዓቀፉ ሕብረተሰብ የሚሰጠውን ዕርዳታ ከፍ እንዲያደርግና የሚሰጠው እርዳታ
በኢህአዴግ ቢሮክራሲያዊ ማነቆ ስር እንዳይወድቅ የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ልዩ ተቋሞች በቂ
ቁጥጥር እንዲያደረጉ አጥብቀን እንጠይቃለን፤

**ኅብረት ኃይል ነው!**

**የኢተፖድኅ አስተባባሪ ኮሚቴ**
**ፍራንክፈርት /ጀርመን**
**የካቲት ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.**